# መርህ - ፖሊሲ

BOARD OF EDUCATION OF
MONTGOMERY COUNTY
የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ

**ተዛማጅ ግብአቶች፡-** BOA-RA, BLB, EIA, EIA-RA
**ኃላፊ ጽ/ቤት፡-** የት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ
ጀነራል ካውንስል

## የህግ አገልግሎት

A. **ዓላማ**

የትምህርት ቦርድ (ቦርዱ) ህጋዊ ጉዳዮችን በሚመለከት ለማማከር እና በህጋዊ ጉዳዮች ላይ ለመወከል የህግ ባለሙያዎች-ጠበቆች የመያዝ መብት እንዳለው ይህ ፖሊሲ በድጋሚ የሚያረጋግጥ እና ብቃት ላለውና ለስኬታማ የህግ አገልግሎቶች ማኔጅመንት አጠቃላይ እቅድም አዘጋጅቷል። የዚህ የህግ አገልግሎት ማኔጅመንት እቅድ ግቦች፣ በተመጣጠነ ወጪ፣ ፈጠራ የተሞላበት፣ እና የሕግ ችግሮችን በቅድሚያ በመከላከል/በማቃለል ረገድ በከፍተኛ የጥራት ደረጃ ቦርዱን፣ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት፣ እና ሌሎች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኞች ህጋዊ መስፈርቶችን ለማሰስ-ለመዳሰስ፣ህጋዊ ተጠያቂነትን መገምገም እና ማኔጅ ማድረግ፣ ሪሶርሶችን እንዳይባክኑ መጠበቅ፣ ክርክሮች በትብብሮሽ ድርድር እንዲፈቱ ማበረታታት እና ከተቻለ፣ ሊወገዱ የሚችሉ ክርክሮችን መቀነስ፣ እና ለሁሉም ተማሪዎች ፍትኃዊ እና አካደሚያዊ ምጡቅነትን ለማስፈን በስትራቴጂያዊ የውሳኔ አሰጣጥ ላይ መሳተፍን ለማመቻቸት ነዉ።

B. **የአተገባበር ስልቶች**

1. የህግ አገልግሎቶች አመራር/አስተዳደር

a) ቦርድ በሚሰጠው መመሪያ፣ እና ከትምህርት ቤቶች ሱፐር ኢንተንደንት ፣ እና ከሌሎች ሃላፊነት የሚመለከታቸው የ MCPS አስተዳዳሪዎች ምክረሃሳብ እና ትብብር መሰረት፣ የ MCPS ጀነራል ካውንስል ለሚከተሉት የሕግ አገልግሎቶች አጠቃላይ አስተዳደር ኃላፊነት አለበት -

(1) በሰራተኛ አስተዳደር ጉዳዮች፣ተማሪዎችን በሚመለከቱ ጉዳዮች፣ ስለ ስፔሻል ኢጁኬሽን፣ ስለ ፖሊሲ ዝግጅት እና ተግባራዊ ማድረግ፣ ስለ ቤት ህንፃ እና መሬትን የመሣሰለ ንብረት አጠቃቀም፣ ኮንትራት እና ግዢ፣ ሰብአዊ መብቶች፣ እና ሌሎችም ከ MCPS አሠራር ጋር ተዛማጅነት የሚኖራቸው ህጋዊ ጉዳዮችን በሚመለከት ወቅታዊ ምክረሃሳብ እና ህጋዊ ምክሮችን መስጠት፤

(2) ቦርድ፣ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት፣ ወይም ሌሎች ሠራተኞች ለ MCPS በሚሠሩበት ወቅት ከሣሾች/ቅሬታ አቅራቢዎች ወይም ተከሣሾች ቢሆኑ ነገር ግን በዚህ ብቻም ሳያበቃ ለስፔሻል ኢጁኬሽን የሚደረግ ህጋዊ ድጋፍን ጭምር በቦርድ ፖሊሲ "Board Policy BLC" መሠረት የሙግት ሁኔታዎችን እና የአመራር ኤጀንሲውን ኩነቶች ወይም ድርጊቶችን በጠቅላላ መቆጣጠር Procedures for Review and Resolution of Special Education Disputes፤

(3) ከዚህ በታች እንደተገለጸው፣ የውጭ አማካሪዎችን የመምረጥ፣ የመምራት፣ የመቆጣጠር ሂደትን ጭምር ቦርዱ በሚሣተፍበት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ሰልፍ ኢንሹራንሽ ፈንድ- Montgomery County Self-Insurance Fund ላይ በመሣተፍ ምክር በመስጠት ከሚያገለግለው የሞንትጎመሪ ካውንቲ ዓቃቤ ህግ ጽ/ቤት ጋር በመተባበር ውስጣዊ እና ከውጭ ህጋዊ አገልግሎት ሰጪዎችን በሙሉ መቆጣጠር እና መገምገም፣

(4) ህጋዊ ሠነዶችን በማርቀቅ፣ በመደራደር፣ ህግን በማስፈጸም፣ እና ኮንትራቶችን፣ ስምምነቶችን፣ እና ከመንግስት ኤጀንሲዎች፣ ሻጮች፣ ኮንትራክተሮች፣ እና የ MCPS ን ትምህርታዊ ተልእኮ የሚደግፉ ሌሎች አካላት ጋር የአፈጻጸም ሠነዶች ላይ ህጋዊ አስተያየት እና ምክር መስጠት፣ እና

(5) ለቦርድ እና ለ MCPS ሠራተኞች ለውሳኔ አሰጣጥ ጠቃሚ የሚሆኑ ህጋዊ ጉዳዮችን አስቀድሞ ማሰብ እና ምላሽ መስጠት፣ የስቴት እና የፌደራል ድንጋጌዎችንና ህግጋትን አንደምታ ውሳኔዎችን ጭምር፣ ቁልፍ የሆኑ የ MCPS ውጥኖችን ይዘት አንደምታ ህጋዊ ምልከታዎችን ማመቻቸት፣ እና የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንትን በማማከር፣ ከለሳ ለማድረግ፣ ለማሻሻል፣ እና የቦርድ ፖሊሲዎችን ከለሳ ለማድረግ የቦርድን ሥራ መደገፍ።

b) የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ከሚመለከታቸዉ ይግባኞች እና ህዝባዊ ችሎቶችን የመሣሠሉ አዳጋች ተግባሮችን፣ በከፊል የፍርድ ቤት ነክ ጉዳዮችን ለመወሰን ቦርዱ ሀላፊነቱን ለማሟላት ህጋዊ ድጋፍ ከሚፈልግባቸው፣ ወይም የትምህርት ቤቶች ሱፐር ኢንተንደንት ስለመቅጠር ከመሣሰሉ ውስን ሁኔታዎች በስተቀር፣ በቦርድ መመሪያ፣ እና የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንትን በማማከር እና በትብብር፣ ጀነራል ካውንስሉ ለቦርድ፣ ለትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት፣ እና ለ MCPS በአጠቃላይ፣ሁሉንም የህግ አገልግሎቶች አስተዳደርን ያስተባብራል።

2. የውጭ ካውንስል መምረጥ፣ መያዝ፣ እና መቆጣጠር

a) የጀነራል ካውንስሉን ሥራ መደገፍ አስፈላጊ እንደመሆኑ መጠን፣ ቦርዱ ካውንስሉን እና የትምህርት ቤቶችን ሱፐርኢንተንደንት ሥራዎቻቸውን የሚደግፍ የውጭ ካውንስል ይኖረዋል። ቦርዱ የሚይዘው የውጭ ካውንስል ሦስት ዋና ሥራዎችን ያከናውናል፡-

(1) ቦርዱ አንዱ ወገን በሆነበት ሙግቶች ዉክልና/መወከል

(2) በአጠቃላይ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሥራ ሂደት ህግ ነክ ጉዳዮችን በሚመለከት፣ ከፍተኛ የህግ ሙያ/ጥበብን በሚጠይቅ የቦርድ ፖሊሲ ወይም ተግባር ጭምር ምክር መስጠት

(3) በይግባኞች እና በሸንጎዎች ቦርዱ ዳኝነት-መሰል ተግባሮችን ሲያከናውን ምክር እና ድጋፍ መስጠት

b) ጠበቃ/ወኪል ከውጪ እንደካውንስል ለመምረጥ ወይም ለመያዝ ትኩረት መሰጠት ያለባቸው እውነታዎች፡- የጠበቃው/ወኪሉ የሥራ ጥራት፣ የበስተኋላ ታሪክ እና ጠቃሚ ልምዶች፣ የህግ ባለሙያነት፣ ስለብዛሃነት እና ስለፍትህ ያለው/ያላት ቁርጠኝነት፣ ለደምበኛው ፍላጎት/ጥያቄ የሚሰማው-የሚሰማት የኃላፊነት ስሜት፣ አኳኋን እና ተደራሽ መሆን፣ ከጥቅም/ፍላጎት ግጭት ነጻ መሆን፣ እና የማኔጅመንት ብቃትና ክህሎት ናቸው።

c) ከትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት እና ከጀነራል ካውንስሉ ጋር በመመካከር፣ የቦርዱን መመዘኛዎች የሚያሟሉ ጠበቆችን ወይም ድርጅቶችን በመለየት እንደውጭ የህግ አገልግሎት ሰጪነት ከቦርድ ጋር ለመሥራት ያላቸውን ፍላጎት እንዲገልጹ ይጋብዛሉ።

d) መስፈርቶቹን ያሟላሉ ተብለው ከተመረጡት ጠበቆች ወይም ድርጅቶች ጋር ወደፊት የሚታደስ መሆኑ ታሳቢ እየተደረገ ቦርዱ ኮንትራት ያደርጋል።

e) ጀነራል ካውንስሉ ስትራቴጂን ከለሣ-ግምገማ ለማድረግ ከውጭ አማካሪ ድርጅት ጋር በቅርበት ይሠራል እና ህጋዊ ጉዳዮችን በሚመለከት በሥራ ላይ የሚውሉ ግብአቶችን ይቆጣጠራል፣ የህጋዊ አቋምን ግልፅነት/ኃሳበ ጽኑነት ማረጋገጥ፣ የወጪ መደራረብን እና ጥረትን/ድካምን ማስወገድ፣ እና ይልቁንም ህጋዊ አገልግሎታቸውን ውጤታማ በሆነ መንገድ በሚከተለዉ አማካይነት ማስተባበር –

(1) ከውጭ ካውንስል ጋር የጽሑፍ ስምምነቶችን ማከናወን፣

(2) ለውጭ ካውንስል የአከፋፈል ሥርአቶችን ደረጃ የጠበቀ መሥፈርት ማዘጋጀት፣

(3) ጉዳዮችን ለመምራት እና ሌሎች ከፍ ያሉ የህጋዊ ጉዳዮችን ፕሮጀክቶች ፕላኖችን ማዳበር እና መተግበርን ጨምሮ ወጪዎችን እና ሠራተኞች ለጠበቆች ያላቸውን ተደራሽነት አመራር፣

(4) በውጭ አማካሪ ድርጅት አማካይነት የሚሰጥ ህጋዊ አገልግሎቶችን በሚመለከት ማናቸውንም ህጋዊ የስነምግባር ጉዳዮች መቆጣጠር እና ተገቢ የሆኑ ምላሾችን ማዳበር፣ እና

(5) ቦርድ እና የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ስለሚጠቀሙት የህግ አገልግሎቶች ጥራት በየጊዜው መመርመር፣ ማጥናት፣ መገንዘብ።

3. ይህንን ፖሊሲ ለማስፈጸም-ለመተግበር የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት መመሪያ-ደንቦችን ያዘጋጃል/ታዘጋጃለች።

C. *ግምገማ እና ሪፖርት*

1. ለውጭ ካውንስል እና የህግ አገልግሎቶች የሚወጡ ወጪዎችን የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት በየወሩ ለቦርድ ሪፖርቶችን ያቀርባል/ታቀርባለች። ቦርዱ ከውጭ ካውንስል ስለሚሰጡት የህግ አገልግሎቶች ጊዜውን ጠብቆ ከኮንትራት ማደስ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ወቅታዊ የግምገማ ሪፖርቶችን ያገኛል።

2. ጀነራል ካውንስሉ፣ ከትምህርት ቤቶች ሱፐር ኢንተንደንት እና ሌሎች የ MCPS ሠራተኞች ጋር በመተባበር፣ ህግን በሚመለከቱ ጉዳዮች አስፈላጊ/ትርጉም ያለው እና ወቅታዊ የህግ አገልግሎት ይሰጣል፣ በቀጠሮ ላይ ያሉ ወይም ከፍተኛ ሙግቶችን ጨምሮ፣ ከ -- ጋር የሚጣጣም Section 3-305(b) የሜሪላንድ የጠቅላላ አገልግሎቶች ደምብ ማዕቀፍ፣ እና ከፍተኛ ባጀት ወይም የፕሮግራም አንድምታዎችን የህግ ጥያቄዎች በሚመለከት ቦርዱን ያማክራል።

3. ይህ ደንብ በቦርድ የማሻሻያ መመርያ መሰረት ይገመገማል።

***ተዛማጅ ምንጮች፡-*** Annotated Code of Maryland, Education Articles §4-104, §4-204, §4-205, and General Provisions Article §3-305(b)። Policy

History: Adopted by Resolution No. 282-85, June 12, 1985; reformatted in accordance with Resolution No. 458-86, August 12, 1986, and accepted by Resolution No. 550-88, October 24, 1988; amended by Resolution No. 210-04, April 15, 2004; amended by Resolution No. 451-09, October 26, 2009; amended by Resolution No 148-20, March 10, 2020.